ጥር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

# ጥያቄያችን ፍትኃዊና አግባብነት ያለው ነው!!
# እነ ፀጋዬ ገ/መድህን(ደብተራው)ና፣ ሌሎች ጓዶቻችን የት ደረሱ?

*" INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE" (SOCEPP)*

ከአያልነሽ

ጥያቄው የእኛ የኢሕ.አፓዎች ጥያቄ ብቻ ሳይሆን፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሊጠይቀው የሚገባ ጥያቄ ነው። "እነ ፀጋዬ ገ/መድህን(ደብተራው) እና ሌሎች ጓዶቻችን የት ደረሱ?" የሚለውን ጥያቄ ኢ.ሕ.አ.ፓዎች እያንዳንዳቸው ሞተዉ ካላለቁ በቀር መቼም ቢሆን የሚጠይቁትና የሚያነሱት፣ የሚያስተጋቡትም ጥያቄያቸው ነው። ጥያቄያችን ዓለም አቀፉን ማህበረሰብም ያካትታል። ጥያቄያችንን ማንኛውም ተቃዋሚ ነኝ የሚል ኃይል ሁሉ እንዲጠይቀው ግዴታ አለበት እንላለን። ጥያቄያችን መቼም ቢሆን መቸ፣ ፍትኃዊና አግባብነት ያለው ጥያቄ ነው።

የጥያቄያችንን ፍትኃዊነት ላብራራ፥

የእነ ፀጋዬ ገ/መድህን (ደብተራውን) ጉዳይ ኢሕአፓዎች የምንመለከተው፣ የት ደረሱም በማለት የያንዳንዳችንን የውስጥ አካላት የሚነዝረን፣ እነኝህ ጓዶቻችን እስከዛሬ በመስዋዕትነት ካጣናቸው ጓዶቻችን በልጠው፣ የተለዩ፣ ወይም "መሪያችን" ስለሆኑ፣ ወይም አንዳንዶቹ እንደሚሉት፣ እነኝህን የምንወዳቸዉንና የምናከብራቸውን ጓዶቻችንን (ታሥረው መዳራሻው አለመታወቁ )እንዳይበቃን፣ በመካከላቸው ልዩነት በመፈጠር፣ ወያኔ ያጠፋቸው/ው "ከእከሌ ዘር በመሆናቸው ወይም በመሆኑ ነው" እያሉ እንደሚያወሩትና እንደሚያስወሩት ሆኖ አይደለም። ለእኛ ጉዳዩ ከዚህ ሁሉ በላይ የሆነ በመሆኑ ነው። የነኝህን የከቡር ጓዶቻችንን ሁኔታ እኛ የኢሕአፓ አባላት ሁሌም ስንቆም፣ ስንሄድ፣ ስንበላ፣ ስንጠጣ፣ ስንተኛ፣ ስንነቃ፣ በጋራ ስንገናኝም ሆነ፣ በተናጠል ስንሆን፣ እንደ ሰው <u>የት ደረሱ?</u> ብለን የምንጠይቀው፣ 18 ዓመት ሙሉ እነኝህ ጓዶቻችንን የበላው የወያኔው አገዛዝ "አሉም፣ የሉምም፣ ገድለናቸዋል፣ አልገደልናቸውም" ብሎ ሊናገር ባለመቻሉና ባለመድፈሩ ነው። ጉዳዩ ለእኛ ለኢሕፓዎች እንኝህ ጓዶቻችንን ወያኔ የት እንዳደረሳቸው ይንገረን፣ ያሳውቀን የሚል ነው። ጥያቄያችን ፍትሃዊና ሰብዓዊ ጥያቄ ነው። ስለ ፍትህ ጉዳይ የምንነጋገረውም ከዚህ በኋላ በመሆኑ ነው። ይሄንን ጥያቄ ደግሞ አጥብቀን የምንጠይቀውና መቼም፣ የትም ቢሆን የምናነሳው ጥያቄ ነው።

ማንም ሰው የሆነ ፍጡር፣ በእንዲህ ዓይነት ከሰውነት በወጣና ከእንስሳና አውሬ ባነሠ መልኩ፣ አንድ ዜጋ ታድኖ መዳረሻው የሚጠፋባትን ኢትዮጵያ፣ ሥርዓት አገዛዟን በፍፁም፣ በፍፁም ልንቀይረው ይገባል ባይ ነኝ። ይሄ ደግሞ *የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጭንቀትና ቀዳሚ ተግባሩ ሊያደርገው ይገባል።* ይህንን መሰል መጥፎ ባህል ይዘን እኛ ኢትዮጵያውያን ሁላችን የኖርንበትና ያለፍነበት በመሆኑ፣ ይሄን *መጥፎ* ባህላችንን ዛሬ ለወለድናቸው ልጆቻችንና ነገ ለሚወለዱት የልጅ ልጆቻችን ልናስተላልፈው የማይገባን፣ አይለጉት ሐኬት እንደሚባለው ነው። ድንቅ የሆኑ፣ ልንኮራባቸው የሚገቡና የተገቡ፣ ኢትዮጵያዊ የሆኑ እሴቶችና ሥነ ደንቦች እንዳሉንና ልንጠብቃቸው ይገባል እንደምንለው ሁሉ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰውን እንዲህ ከእንስሳ በታች አውርዶ፣ <u>በአስተሳሰቡና በእምነቱ ብቻ</u> እንደአውሬ የሚታደንበትን፣ ሥርዓትና መጥፎ ባህላችንን መጥፎ ነው ብለን ደፍረን ለንናገር ይገባል። በተጨማሪም መጥፎነቱን ተቀብለን በሀገራችንም ሊኖር የማይገባ ጉድፋችን መሆኑን በማስመር፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በድፍረት ሊያወግዘውና ልናውግዘው፣ ብሎም ለመቀየርና መልክም ልናስይዘው ይገባል ባይ ነኝ - በምድር ላይ ከሰው ልጅ የበለጠ ክቡር ነገር የለምና። እኛ ሰው የተባልን ፍጡሮች የሰውን ልጅ ክቡርነት ከዚህ በታች አውረደን መመልከት ከጀመርንና ይሄንንም ለመድነው ልብስ ካደረግነው በእውነቱ "ሰውነታችን" ጥያቄ ውስጥ ይገባል ባይ ነኝ።

አንድ ኢትዮጵያዊ/ት በፓለቲካ አመለካከቱና አስተሳሰቡ ብቻ ታድኖ የሚታሰርበት፣ የሚገደልበት፣ በፓለቲካ አስተሳሰቡ ብቻ እስር ቤት እንዲበሰብስ የሚደረግበትና የሚወረወርበት "ዕድሜ ልክ" ተብሎ የሚፈረድበትን ሥርአተ-ኢትዮጵያ አገዛዝሏንና አስተዳደሯንም፣ በርግጥም፣ በእርግጥ ከምር ታግለን መቀየር አለብን። በእኔ ዕምነት ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ሰው በፓለቲካ እምነቱ ሳቢያ መታሠር፣ መገደል፣ መጋዝ፣ መሰደድ፣ ማስፈራራትና እንዲበረገግ መደረግ አይገባውም ባይ ነኝ። እንደኔ እንደኔ ቀድሞ ነገር <u>ኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ እሥር ቤት መኖር የለበትም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ እስረኛ የሚባል ነገር ሊኖር አይገባምም።</u> እጅግም ልናፍርበት የሚገባ መጥፎ ባህላችን ነው - ሰው እንዴት በነፃ አሰበ፣ ተመራመረ፣ ጠይቀ፣ ዘፈን፣ ተቼ፣ ተብሎ ወደ እስር ቤት ይወረወራል? ሰው እንዴት በፓለቲካ ዕምነቱ ይገደላል? ትናንትና <u>"ያሰበ፣ ያሳሰበ፣"</u> በሚል አዋጅ እኮ አንድ ትውልድ ተቀጥፎ ለዛሬው ግፋችን ያደረሰን የቅርብ ጊዜ ሰቀቀናችን ነው። ወገኖቼ! እንዲህ ዓይነት "ሥርአታችንን" እንዲህ ዓይነት እስር ቤቶችን አፈራርሰን፣ እንዲህ ዓይነት ተቋሞችን ነቃቅለን ወደ ት/ቤት ልንቀይራቸው ይገባል ባይ ነኝ - የመጥፎ ባህል ተምሳሌዎቻችን ናቸውና!

ማንም ኢትዮጵያዊ የሰውን ልጅ ክቡርነት የሚያምንና እቀበላለሁ የሚል ሁሉ ደግሞ፣ የእነፀጋዬ(ደብተራው)ንና የሌሎች የኢሕአፓ ጓዶቻችንን መዳረሻ ሳይጠይቅ፣ እንደተራ ነገርና እንዳልባሌ ዕቃ በአርምሞና በፀጥታ ሊያልፈው አይገባም። ማንኛውም የፓለቲካ ደርጅትም ጥያቄውን አይቶ እንዳላዬ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ አድርጎ ማለፍ የማይችለው፣ እፊቱ እነሆኝ ብሎ የቀረበለት የጊዜው ፈተና ነው። የጥያቄው ክብደትና ዚቅ ይሄ ነው።

ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው የወያኔ/ኢህዴአግ አገዛዝ ኢትዮጵያን ከጠቆጣጠረ ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ፣ የእነፀጋዬ ገ/መድህን (ደብተራው) እና የሌሎች ጓዶቻችንን ጉዳይ ሊናገር አልፈቀደም። የጥያቄያችን ዋና መሠረቱ <u>ወያኔ ስለእነ ደብተራው ለምን ሊናገር አይፈልግም? ገድሏቸዋል? እንዳሰራቸዉ ነው? ገድሏቸው ከሆነም መቼ፣ እንዳሰራቸው ከሆነም የት ነው የታሰሩበት ቦታ? የት ውስጥ ነው የከተታቸው?</u> ለነዚህ ጥያቄዎች ቢያንስ ለቤተሰቦቻቸው መልስ መስጠት ዓለም አቀፉ ሕግም ያስገድደዋል። ስለዚህ እነደብተራውን የት ናቸው? ወያኔ የት አደረሳቸው? ለሚለው ጥያቄ መልስ እስከናገኝ ድረስ የማንተወው ጥያቄያችን ነው።

ጥያቄያችን ከሕግ ሆነ፣ ከሥነ ደንብ (ሥርዓት) አንፃር በየትኛውም አግባብ ፍትኃዊ ጥያቄ ነው፤ ከሕግ አንፃርም ቢሆን እነ ደብተራውን የያዘው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ፣ ምንም ይሁን ምን "ሕግ" አለኝ ብሎ አገር እየገዛ ነውና፣ አገር እገዛበታለሁ በሚለው "ህጉም" እንኳ 18 ዓመት ሙሉ ወደ ፍትህ ደጅ ማቅረብ ቀርቶ ስለመያዛቸውም ሊናገር አልፈቀደም። እነ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን በሌሉበት "ፍትሕ" ደጅ አቀረብኩ የሚለው ወያኔና የወያኔ ኢትዮጵያ፣ እንዴት የእነፀጋዬ ገ/መድህን(ደብተራው) እና ጓዶቻችችን ጉዳይ መዳረሻቸው ሳይታወቅ ተዳፍኖ ይቀራል? እንዴት ኢትዮጵያዊው ዜጋስ ይሄንን ኢፍትሃዊና ኢሰባዓዊ የሆነ ድርጊት እየሰማ! እያየዬ በዝምታ አቀረቀረ?

እንዴት? እነቀልቤሳ ነገምን፣ እነመላኩ ተፈራን ወደ "ፍትህ" አቀረብኩ ያለው ወያኔ፣ የእነደብተራውን ስም ሆነ ሞትና ሕይወት ላያነሳ መኃላ ገባ? አሁንም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ይሄንን ጥያቄ ለምን አይጠይቅም? ምነው የነፀጋዬ (ደብተራውን)ና የሌሎቹም ሰዎቻችን መዳረሻ ጠፍቶ፣ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ሁሉ ዝምታን መርጦ አደፈጠ? ከቶ ለምን ይሆን? ጥያቄውና ጥያቄያችን ለአገዛዙ ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ/ት የምናነሳው ጥያቄ ነው። ዛሬ በኢትዮጵያችን ሰለ ሠላም፣ ስለ እርቅ፣ ስለ ፍትህ፣ ሊሰብክና ሊያስተምር፣ ዛሬ ስለ ፍቅር ቅዱስነት ሊያስረዳ፣ ስለ ሰው ልጅ ክቡርነት ሊገልፅ ለሚጥር ኢትዮጵያዊ ወገን፣ ጆሮአችንን አናውስም፣ አንሰጥም ብንል *ይከፋው/ት* ይሆን ? ለምን ይከፋዋል/ታል? በእኛ እምነት፥

"በየትም ቦታ በማንም ላይ የሚፈጸም ኢፍትሃዊነት፣ በሁሉም ቦታ በሁሉም ላይ እንደሚፈጸም መታየት አለበት" በሚለው ስለምናምን፣ በኢትዮጵያችን ይህ ለተፈጸመበት ማንኛዉም ሰው እየጮህንና እየታገልን ድርጊቱም ኢፍትሃዊነት መሆኑን ስናጋልጥ ኖረናል፣ አሁንም ማጋለጣችን አናቆምም። ነገር ግን ከሰው ልጅ ክቡርነት አንፃር ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንም ሰው ያለ አግባብ ኢ-ፍትኃዊና ኢ-ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለመታሠሩ፣ ለመንገላታቱ፣ ለመሳደዱ፣ ለመጋዙ፣ ከሀገሩ እንዲወጣ በግድ ለመገፋቱ ሁሉ አግባብ አይደለም ብሎ የሚያለቅሰውና የሚጮኸው ሁሉ በእውነት ሁሉም ከልቡ ነውን ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ ምን ይሆን?

በሆነ አጋጣሚ የታሠሩት ይፈቱ ለማለት በየጊዜው በሚወጣ የሠላማዊ ሠልፍ አደባባይ ላይ፣ እነፀጋዬ (ደብተራውን)ና የሌሎች ጓዶቻችንን ስምና ምስላቸውን ለመያዝ ያልደፈረ ኢትዮጵያዊ፣ እነስዬ ጋር አብራችሁ በሕብረት ለመሥራት ሞክሩ ብሎ አማላጅ ለመሆን ምንስ የሞራል ብቃት ይኖረዋል? ስለ እነአነግ፣ ስለ እነአብነግ የታሰሩና የጠፉ ሰዎች ሰልፍ የወጣ ኢትዮጵያዊ/ት፣ የነ ፀጋዬ/ደብተራውን ፎቶ ይዞ ለመውጣት ለምን አፈረ? ለምንስ እስከዛሬ ያከራከራል? ወዘተ፣ ወዘተ. . . ተብሎ መጠየቅ ያለበት መሠረታዊና አብይ ጥያቄ ነው።

ወያኔ የቀድሞ የደርግ አባሎችን በቀይ ሽብር ከሶ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ ባደረገበት (እነ ፕሮፌሰር መሥፍን ቀርበው በችሎቱ አደባባይ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡበትን) የተመለከተና የተከታተለ ኢትዮጵያዊ፣ ከቀይ ሽብሩ ሰለባ የተረፉትን እነፀጋዬ (ደብተራው)ን ፀረ-ኢትዮጵያው የሆነው ወያኔ ሲሰውራቸው፣ ኢትዮጵያዊው ሁሉ ምነው የዝሆን ጆሮ ይስጠኝን መረጠ?

የተከበራችሁ አንባቢዎች! ሆይ

እነ ፀጋዬ/ደብተራውና ሌሎች ጓዶቻችን የት ደረሱ? ብለን መጠየቃችንን የማናቆመውና የምንቀጥልበት፣ ከላይ ላነሳው እንደሞከርኩት እደግመዋለሁ፣ ከኢሕአፓ ውስጥ እነርሱ የተለዩ ሆነው ወይም ፀጋዬ (ደብተራው) "መሪያችን" ስለሆነ አይደለም። በነገራችን ላይ ኢሕአፓ ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ድርጅቱ የሚሰራበትና፣ የሚጠቀምበት የአሠራር መርህ፣ የጋራ አመራር ኮሚቴ አሠራርን ነው። አዎ! እርግጥ ነው ፀጋዬ (ደብተራው) የድርጅታችን የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል ከነበሩት ውስጥ አንዱ ነው። ነገር ግን የእነፀጋዬ (ደብተራው)ን ጉዳይ ዛሬም ልዩና ይበልጥ መሪር የሚያደርገው፣ መቼም ቢሆን የምንጮኸበቱ ምክንያት፣ የእነፀጋዬን መዳረሻ አብረው ያጠፉት፣ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ ህግ ሁሉ ፅፈው ያፀደቁት፣ እነስዬ አብርሃና ገብሩ አስራትን የ"ክብር እንግዳ" በምናደርግበት እውነታ ላይ፣ ዛሬ እነስዬ ከወያኔ ጋር ተጣልተን ወጣን ባሉበት፤ "ፀረ ኢሕአዴግ" ትግልም እያደረግን ነው በሚሉበት ጊዜ፣ አሁንም ስለ እነፀጋዬ ጉዳይ ሊነግሩንና ሊተነፍሱ አለመፈለጋቸው ነው። የእነ ስዬው "መድረክ"ና የእነገብሩ አስራት "ዓረና" የተባለው ድርጅት ስለ ፍትህ መዛባት በቅርቡ ያወጣው መግለጫ እንዲህ ይነበባል።

> "ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ተይዘው ሕግ ፊት መቅረብ ካለባቸው በህጉ አግባብ ከፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ አውጥቶ መሆን ሲገባው ማንነታቸዉን ባላሳወቁና ሕጋዊ መጥሪያ ባላሳዩ ኃይሎች ተገደው እየተንገላቱ መወሰዳቸው የሕግ የበላይነትን የጣሰና በብዙ ወገኖችም ዘንድ ሥጋት የጫረ እርምጃ መሆኑ በሀገራችን ያለው ሁኔታ እጅግ አሳዛኝና አሳሳቢ ያደርገዋል..."

የእነስዬ "መድረክና" የእነገብሩ አስራት "ዓረና" አንድ ላይ ያወጣው ይህ ከላይ የተቀመጠው የሚያማልል መግለጫ "ስለ ሕግ የበላይነት" መጣስ የሚያወሳ ነው። በመሠረተ- ይዘቱ በማንኛውም አገር ሊሠራበት የሚገባና በተለይም በአደጉና በኢኮኖሚ በበለፀጉ ሀገሮችም ዘንድ በተግባር፣ ሥራ ላይ የዋለ የፍትህ ሂደት ቢሆንም፣ ይሄ እነ ስዬና ገብሩ አስራት ዛሬ ሊራቀቁበትና ሊነግሩን የሚፈልጉት የፍትህ መጣስ ጉዳይ፣

የአፋቸው መፍቻ ባዶ ቃል አድርገውት እንጂ፣ ዛሬም በተግባርና በልባቸው ህግና ፍትህን በጫማቸው ሥር ጨፍልቀው ለመጓዛቸውና ለመኖራቸው፣ የእነፀጋዬ (ደብተራው) ጉዳይ አንዱ ቋሚ ምስክር ነው። ኢትዮጵያንና ህዝቧን ወደ መቀመቅ ለማውረደ የነደፉትን መርሃ ግብራቸውን እንኳ ተቀምጠውና መርመረው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ ለማለት ባልደፈሩበት ሁኔታ፣ እነስዬ/ገብሩ አስራትን እንዴት ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ሁሉ ይሄንን ጥያቄ ሳይጠይቃቸው ለማለፍ ይዳዳል? እንዴትስ አይጠይቀውም?

በ1983 ዓ.ም. በወያኔ ተይዘው የተሰወሩትና መዳረሻቸውን ያላወቅነው እነኝህ ጓዶቻችን፣ ከ1967 ዓ/ም ጀምሮ ከተራ አባልነት እስከ ተለያዩ የሐላፊነት እርከኖችና ከፍተኛ የድርጅቱ የኃላፊነት ቦታ ሁሉ ተመድበው ሲሰሩ፣ ያለማሰለስ በቆራጥነት ሲታገሉና ሲያታግሉ የቆዩ ክቡርና እንቁ ጓዶቻችን ናቸው። በርካታዎቹም ከ1966 አብዮት በፊት ጀምሮ በተማሪው እንቅስቃሴ ጭምር ከፍተኛን አስተዋጽኦ ያደረጉ ነበሩ። በወያኔ ታድነው የተሠወሩት የእነኝህ ክቡርና ወርቃማ ጓዶቻችን ስም ዝርዝር እንደሚከተለው አቀርቤዋለሁ።

1. ፀጋዬ ገ/መድህን (ደብተራው) - የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል (1983 ዓ.ም በወያኔ ተይዞ መዳረሻው ያልታወቀ፣)
2. ይስሐቅ ደብረ ፅዮን (አበበ) - የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ የነበረ፣ (1983ዓ.ም መዳረሻው ያልታወቀ)
3. በለጠ አምሐ (ገብረ ኢየሱስ) የከፍተኛ አመራር አባል የነበረ፣ (1983 ዓ.ም በወያኔ ተይዞ መዳረሻው)
4. ስጦታው ሁሴን (ታደለ) የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ የነበረ፤ (1983 ዓ.ም በወያኔ ተይዞ መዳረሻው)
5. ሐጎስ በዛብህ (በርሔ) የሠራዊት አመራር ኮሚቴ አባል የነበረ፤ (1983 ዓ/ም በወያኔ ተይዞ መዳረሻው)
6. ተኸላይ ገ/ሥላሴ (አሉላ) የሠራዊቱ የቀጠና አመራር አባልና የቡዙሃን ድርጅት ኮሚቴ አባል የነበረ (በ1983 ዓ.ም በወያኔ ተይዞ የተሰወረ)
7. ደሳለኝ አምሳሉ (አበራ) የሠራዊቱ የቀጠና አመራር አባልና የብዙሃን ድርጅቶች ኮሚቴ አባል (በ1983 ዓ.ም በወያኔ ተይዞ የተሠወረ)
8. አበራሽ በርታ (መዓዛ) የሠራዊቱ የፖለቲካና የፕሮፓጋንዳ ክፍል ኮሚቴ አባል የነበረች (1985 ዓ.ም አዲስ በአበባ በወያኔ ተይዛ የተሰወረች)
9. ተስፋዬ ከበደ (አቡሃይ) ሀኪም የነበረ (በ1983 ዓ.ም በወያኔ ተይዞ ከተፈታ በኋላ ተመልሶ በ1985 ዓ.ም በአዲስ አበባ ተይዞ የተሰወረ፤)
10. ለማ ኃይሉ - (በ1983 ዓ.ም በሜዳ ተይዞ ከተፈታ በኋላ ተመልሶ በ1985 በአዲስ አበባ ተይዞ የተሰወረ፥)
11. ወንዱ ሲራክ
12. አበበ አይነኩሉ (1983 ዓ.ም ጎጃም በወያኔ ተይዞ የተሠወረ)
13. ቱሉ (በ1983 ዓ.ም ከሱዳን ተይዞ ባህርዳር ታስሮ ከቆየ በኋላ የት እንዳደርሱት ያልታወቀ፤ ሌሎችም በርካታዎች የኢሕአፓ አባላት ወዘተ. . .

እነኝህ ስማቸው ከዚህ በላይ የተዘረዘረውና ሌሎች ስማቸው ያልተገለጸ በርካታ የኢሕአፓ አባላት እነስዬ አብርሃና ገብሩ አስራት በወያኔ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል፣ ስዬ ደግሞ የጦሩ ዋና አዛዥ ሆነው በሚያገለግሉበት ወቅት፣ ይዘው የሰወሯቸው ጓዶቻችንን ናቸው። ለዚህም ነው ዛሬ እነስዬ ስለ ሠላምና እርቅ ለማውራትና ለመስበክ ድፍረቱን ካገኙ፣ ለዕርቅ እንድንበቃ ከተመኙ፣ ቢያንስ የእነኝህን ጓዶቻችን መዳረሻ ሊያሳውቁንና ማሳውቅም ግዴታቸው የሚሆነው። በወያኔ እየታደኑ ደብዛቸው የጠፋው ጓዶቻችን በሙሉ ከአመራር እስከ ተራ አባላት የነበሩትን ሁሉ ያካተተ ነው። በኢሕአፓ ውስጥ ከትልቅ እስከ ትንሿ የኃላፊነት ቦታ ተመድቦ መሥራት ማለት፣ ኃላፊነት እንጅ ሹመት አይደለም። በኢሕአፓ ውስጥ፣ በአባልነትም ሆነ በኃላፊነት ተመድቦ መሥራት ማለት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብቱና እንዲሁም ኢትዮጵያ፣ በነፃነትና በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ትተዳደር ዘንድ ለሚያደርገው ትግል አስተዋጾአ ለማድረግ

የሚሠለፉበት ግዴታ እንጅ፣ በእዬኮፒተሩ መስኮት ፎተግራፋቸውን እየለጠፉ የሚነግዱበት የፓለቲካ ቁማር አይደለም።

ለኢሕአፓ የ አንድ አባል መጥፋትና አንድን አባል በመስዋዕትነት ማጣት፣ ብዙ አባሎችን እንዳጣ ነው የሚቆጥረው፣ ውስጡንም እንደቁስል ነው የሚጠዘጥዘው።

ኢሕአፓ በታሰሩና በተሰው አባሎቹ፣ ሁሌ እርር ኩምትር የሚለው ለምን ሞቱ፣ ለምን ተሰቃዬ በሚል በሞታቸው ለማዘን፣ በስቃያቸው ደግሞ ለመቆዘም ሳይሆን፣ ኢትዮጵያን በማዳኑ ተጋድሎ ላይ ዛሬም ሆነ ነገም ሊጫወቱና/ሊያበርከቱ የሚችሉትን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ኢሕአፓ አንድን ጓድ/ጓዲትን ሲያጣና፣ በተሰዋው/ቸው 1 ጓድ ውስጥ ብዙ ጓዶቹን አብሮ ስለሚያጣ ነው።

1 ጓዳችን ሣሙዔል ሲሰዋ የተሰዋው አንድ ሣሙዔል ብቻ አይደለም፣ በውስጡ ብዙ ሳሙዔሎችን ይዞ ነው የሚሄደው/የሚሰዋብን፤ አንዱን ጓዳችን ኃይምን ስንነጠቅ አንድ ኃይምን ብቻ አይደለም የምናጣው በውስጡ ብዙ ኃይሞችን ይዞ ስለሚሰዋብን ነው። ለኢሕአፓ እያንዳንዱ አባል/አባላት እጅግ ውድ ናቸው።

የኢህአፓ አባላት እያንዳንዳቸው ለድርጅታቸው ለኢሕአፓ ሁሉም፣ አመራርም አባልም ናቸው። ሁሉም በፍላጎታቸው ለሐገራቸው ኢትዮጵያ ለመሰዋት ሲዘጋጁ ከልባቸው በፍቅር፣ ከምርም አምነውበትና ስለሚያምኑበትም ጭምር ነው። ይሄንን ሐቅ ደግሞ እንኳንስ ወዳጅ የሆነ ቀርቶ፣ ጠላት አድርገው ሊያጠፉት ብዙ የደከሙትና እስካሁንም የሚደክመው ወያኔ ራሱም አልካደውም/አይክደውም። መንግሥቱ ኃ/ማርያም ስለ ኢሕአፓ ጽናትና አይበገሬነት (የድርጅታቸውን ምስጢር ላለማውጣትና ጓዶቻቸውን አሳልፈው ላለመስጠት ራሳቸዉን ሲሰዉ፣ ለኢትዮጵያ ባላቸው ፍቅርም ለሞሞት ያሳዩትን ጥልቅ ስሜትና የሚንቦገቦግ ቁጣ) የተመለከተ ነበረና፣ ስለ አይበገሬነታቸው "የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ትዝታዎች" በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ሳይጠቅሰው አላለፈም፡፡

ወያኔም ቢሆን ከ1968 ዓ/ም ኢሕአፓና ወያኔ ከተዋወቁበት ጀምሮ ያሳለፍነውን ጊዜ ሲናገር "ለትልቂቱ ኢትዮጵያ" የሚታገል ትምክህተኛ ብሎ ኢሕአፓን "አባይ ኢትዮጵያ" የሚል ስም ሰጥቶታል። ይሄው እስካሁንም ድረስ ወያኔና ኢሕአፓ ጠባቸው መሠረታዊና፣ በኢትዮጵያ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይም የማይታረቅ/የማይቀራረብ ቅራኔ ያላቸው ለመሆኑ ፀሐይ የሞቀው ሐቅ ነው። ለዚህም ነው ኢህሕአፓን፣ ከኢትዮጵያ ኢትዮጵያን ደግሞ ከኢሕአፓ ለይቶ ማየት እጅግ የሚከብደው።

ለዚህም ነው ለኢሕአፓ ሐገር የት ነው ሲባል ኢትዮጵያ፣ ዘርህ/ሽ ሲባል ኢሕአፓ ይላሉ የተባለላቸውና የሚባልላቸው። በኢሕአፓ ውስጥ ገብቶ ለመታገል ቁልፉ ጥያቄ፣ በፍላጎት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን በመቆም የኢትዮጵያ ህዝብ በሚያደርገው የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግል ተጋድሎ በአይብገሬነት፣ በጽናት ከጎኑ ቆሞ ለመታገል የሚጠይቀውን መስዋዕትነትም በፈቃደኝነት ለመቀበል ቃል መግባት ብቻ ነው። ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ መሞትን ደግሞ ጌጣችን ነው ብለን የምንኮራበትና የምንቀበለው ነው። አበቃሁ! ቺር ይግጠመን።

**የሕዝብ ድምፅ ይከበር! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ!**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

**"INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE"**

ጃኑዋሪ 19/ 2009